# ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አያድርም

## ትዕይንት አንድ

1. ከአንድ ሰፈር ውስጥ

1.1 / አንድ ዘመናዊ የግንብ አጥርና የብረት በር ያለው ግቢና ከአጠገቡ በቆርቆሮ እና በእንጨት የታጠረ እና በቆርቆሮ የተሰራ የግቢ አጥር ያለው ግቢ በራቸው እንደ ተዘጉ ከውጭ ይታያሉ።/

1.1.1 / የቆርቆሮው የግቢ በር ሲከፈት ይታያል/

አቶ ማሩ -/ የበሩ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ኢትዮጵያዊ የሆነ የአባ ወራ አለባበስ ለብሰው ከግቢያቸው ውስጥ የቆርቆውን በር ከፍተው ይወጡና ቆም ብለው የወጡበትን በር እየዘጉ ግራና ቀኙን እያማተሩ ያዩና ወደ ጎን ዞረው የግቢያቸውን አጥር እየታከኩ መሄድ ይጀምራሉ።/

ወጣት ኤደን - / አባቷ አቶ ማሩ የወጡበትን በር በመጣደፍ ከፍታ እየወጣች አባቷ ወደ ሄዱበት ዞራ በሩጫ እርምጃ እየሄደችና እየጠራቻቸው ታስቆማቸዋለች።/ ይህች ወጣት በፀጉሯ (ረጅም ፀጉር) ላይም ሆነ በገጿ ላይ ምንም ዓይነት ሜካፕ የማይታይ ቆንጆ ወጣት ናት።

ሄኖክ - / እድሜው በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ የኤደን ታላቅ ወንድም ሲሆን ኤደንን ተከትሏት ከግቢው ይወጣና ኤደን ከአባቷ ጋ ደርሳ ማውራት መጀመሯን ሲመለከት አባቱ እንዳመለከቱት ደንገጥ ብሎ ወደ መጣበት ተመለሰ። በመደበቅ አንገቱን እያሰገገ ያያቸዋል።/

ኤደን - / በፍርሃት ስሜት ፀጉሯን በጣቶቿ እያፍተለተለች እና በገጿ ላይ መማጸን እየተነበበባት አባቷን ገንዘብ እንዲሰጧት በመጠየቅ ዓይነት ታናግራቸዋለች።/

አቶ ማኑ – / ፊታቸውን ኮሶ እንዳስመሰሉ ካዳመጧት በኋላ በብስጭት እየተወራጩ እና ኪሳቸውን እየጠቋቆሙ ገንዘብ እንደሌላቸው እየተናገሩ ልጃቸውን በቆመችበት ጥለዋት እየተጣደፉ ሄደው ይሰወራሉ።/

ኤደን – / በቆመችበት እንዳዘነች ቆማ እያሰበች አባቷን በዓይኖቿ እየተከተለች ቆይታ ወደ መጣችበት ዞራ እንዳቀረቀረች ትራመዳለች።/

ሄኖክ – /የአባቱን መሰወር እንደ ተመለከተ ከተደበቀበት ወጥቶ ወደ ኤደን ሄዶ አባቷ ወደ ሄዱበት እየተጠቋቆሙ የፈለጉትን ባለማግኘታቸው በመቆጨት ማውራት እንደ ጀመሩ (የጎረቤታቸው የግቢ በር ሲከፈት በመስማቱ ዞሮ ይመለከታል።/

1.2 / ከዘመናዊው የግቢ በርና ከግቢው ውስጥ/

1.2.1 / ከውጭ ወደ ግቢው ውስጥ እየታየ የግቢው በር በቤት ሰራተኛዋ ተከፍቶ ሲያበቃ ከግቢው ውስጥ ቆማ የነበረችው ዘመናዊ የቤት መኪና ከቆመችበት ተንቀሳቅሳ ከግቢው መውጣት እንደ ጀመረች ከመኪናዋ ጀርባ ያለው የዘመናዊው መኖሪያ ቤት ውጪው ገጽታ እየታየ የሳሎኑ በር ተከፍቶ ጳውሎስ እየተጣደፈ ይወጣና በአንድ እጁ የጥሪ ድምፅ በማሰማት ላይ ያለችውን የሞባይል ስልክ ይዞ ከግቢው ውስጥ በመውቋሮት ላይ ያለችውን የአባቱን መኪና ተከትሏት እየሮጠ መሄድ እንደ ጀመረ ታናሽ እህቱ መዓዛ ስትወጣ ትታያለች።/

/ ጳውሎስ የመዓዛ ታላቅ እና የጎረቤቱ የሄኖክ የእድሜ እኩያ ሲሆን፥ መዓዛም የኤደን እኩያ ስትሆን ጳውሎስ እና መዓዛ ከነሄኖክ በተደላደለ ኑሮ ውስጥ የሚኖሩ ከመሆናቸውም በሰውነታቸው ላይ ምቾት የሚታይባቸው እና በአለባበሳቸው እና በጸጉር አሰራራቸው የተሽቀረቀሩ ሲሆኑ በመዓዛ ገጽ ላይ የተጠቀመችው ሜካፕ እናየተሰራችው ጸጉሯም ከኤደን የተለየች አድርጓታል።/

1.3 / ከግቢው ውጭ/

/ጳውሎስ ከላይ መሮጡን እንደ ቀጠለ ከግቢው በር ብዙም ያልራቀችውን የአባቱን መኪና አስቁሟት በሹፌሩ በር በኩል ባለው በመኪናዋ የበር መስኮት ጎንበስ ብሎ የጥሪ ድምጽ ማሰማት ያቆመችውን የሚባይል ስልክ በግራ እጁ ወደ ኋላው ደብቆ ከአባቱ ጋር መነጋገር ሲጀምር ይታያል።/

1.3.1 / ሄኖክና ኤደን ከግቢያቸው በር ጋ ደርሰው እንደ ቆሙ ወደ እነ ጳውሎስ በሞቀ ፈገግታ እየተመለከቱ ሳለ መዓዛም ጳውሎስን ተከትላ ከግቢያቸው ውስጥ ስትወጣ ያያትና ሁለቱም ወደ መዓዛ እየሄዱ መዓዛም ወደ እነሱ እየመጣች በሞቀ ፈገግታ እየተያዩ ሰላምታ ሲለዋወጡ ይታያሉ።/

/ ጳውሎስ በግራ እጁ የሞባይል ስልኩን ከኋላው አድርጎና ደብቆ እንደያዘ የቀኝ እጁን ወደ አባቱ ዘርግቶ ሁለት ድፍን የመቶ ብሮች ሲቀበልና በአንጻሩ የደበቀውን የሞባይል ስልክ ለአባቱ ካሳየ በኋላ እየሳቀ ስልኩን ይሰጣቸውና መኪናዋ መንቀሳቀስ ስትጀምር እሱ ወደ ሄኖክ ዞሮ ይሄድና በሞቀ የጓደኝነት ስሜት እየተቃቀፉ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እንደ ተቃቀፉ ጎን ለጎን ሆነው ከሚያወሩት ከነ መዓዛ ተለይተው ወደ እነ ጳውሎስ ግቢ ሄደው ይገቡና ይሰወራሉ።/

/ ሂሩትና መዓዛም እየተሳሳቁና እያወሩ መኪናዋ ወደ ሄደችበት ያመራሉ።/

# ትዕይንት ሁለት

2. ከአቶ ማሩ መኖሪያ ቤት ውስጥ

2.1 በጅምሩ የቤቱ መጪው ገጽታ ይታያል

2.2 ከምግብ ቤቱ ውስጥ

2.2.1 በጅምሩ የምግብ ቤቱ ጠረጴዛ ላይ በመሶብ የተሸፈነው ትሪ እየታየ ኤደን መሶቡን ታነሳዋለች። በቅርበት እየታየ ሁለት የጥቁር ጤፍ እንጀራዎችን የያዘ ትሪ በኤደን እጅ መሶቡ ተይዞ እንደ መጣ ሲቀመጥ በቅርበት ይታያል (በመሶብ የተከደነ ትሪ)

ኤደን - ትሪውን አስቀምጣ ከሄኖክ ፊት ለፊት ካለው ወንበር ላይ ትቀመጣለች፡፡

ሄኖክ - አስቀድሞ ከተቀመጠበት ቦታ ሆኖ በትሪው ላይ የቀረበውን እንጀራ ፊሩን ኮሶ አስመስሎ በቀኝ እጁ በትሪው ላይ ካሉት ሁለት እንጀራዎች የላይኛውን ቀንጥሶ እያነሳ በጥላቻ ያየውና ይለቀዋል፡፡

ወ/ሮ ጌጤ - የእነ ሄኖክ እናት ሲሆኑ ከጓዲያው በኩል በሳህን ወጥ ይዘው እንደ መጡ ከእነ ሄኖክ መሀል ካለው ወንበር ላይ ይቀመጡ እና ከሳህኑ ውስጥ ያለውን የምስር ወጥ በጭልፋ እየዘገኑ ከትሪው ላይ ካለው እንጀራ መሀል ያፈሳሉ፡፡ አንድ ጊዜ አፍሰው ሁለተኛ ሊደግሙ ሲሉ…

ሄኖክ - አቋርጧቸው ፊቱን ኮሶ አስመስሎ ወጡንም ሲመለከት በመበሳጨት ኧ.ረ.እ.ማ.ዬ

ጌጤ - ለሁለተኛ ጊዜ ከሳህኑ ውስጥ መጨለፍ የጀመሩትን ወጥ በመደናገጥ እየመለሱት ወደ ሄኖክ ቀና ብለው በእናትነት ስስት እያዩት ውይ በሞትኩት ምን … ምን ሆንኩኝ?!

ሄኖክ - ወደ እንጀራው እየጠቆመ እ-ህ- ዛሬም የምስር ወጥ አይሰለችም?

ኤደን - ወደ እንጀራው እየጠቆመች በመከፋትና በንቀት በዛ ላይ በጥቁር እንጀራ

ጌጤ - በትህትና ሁለቱንም እያዩአቸው ኧረ ተመስገን ነው የሚባለው ልጆች! ሳህኑን እያስቀመጡ

ሄኖክ - እንደ መቆጣት ኧረ በፈጠረሽ እ. ማ እሩቅ እያለመና እያሰበ እኔ እሺ ይህንን ምሳ ነው ብዬ በልቼ ከምውል ት. ና. ን. ት. ና እሩቅ እያለመ ማሰብ ሲጀምር ፊቱ ከርቀት እየቀረበ ይታያል፡፡

# ትዕይንት ሦስት

3. ከእነ ጳውሎስ ዘመናዊ መኖሪያ ቤት ምግብ ቤት

3.1 በጅምሩ ከምገብ ቤቱ ጠረጴዛ ላይ በመነሳት ከጠረጴዛው መሀል ላይ የተለያዩ ወጦች እና ጥብሶች ከያዙ ሳህኖች ውስጥ የሄኖክና የጳውሎስ የቀኝ እጆች ከሳህኖቹ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ጭልፋና ማንኪያዎች በመፈራረቅ እያነሱና

እየመለሱ በግራ እጆቻቸው ከያዟቸው የመመገቢያ ሳህኖች ሲያደርጎ እጆቻቸው

በቅርበት ይታያሉ፡፡

ከጠረጴዛው ላይ ካሉት ሳህኖች በተጨማሪ የለስላሳ መጠጦች እና በፍራፍሬዎች

የተሞላ ትሪም ይታያል፡፡

# ትዕይንት አራት

/ ከላይኛው ከአቶ ማሩ ምግብ ቤት ውስጥ/

ሄኖክ - ትዝታው ከፊቱ ላይ እየራቀ ሲሄድ ፊቱ ከቅርበት እየራቀ መታየት ይጀምራል

ወ/ሮ ጌጤ - በምጸት ፈገግ እያሉ አ. ሃ እናስ አንተ!?

ሄኖክ - ትሪውን በጥላቻ እያየ እናማ በቃ… ይሄንን ምሳ ነው ብዬ በልቼ የበላሁትን መክሰስ

እያሰብኩኝ … ተጠቅልዬ ማ. ደ. ር!! በቃ!!

ጌጤ - በንዴት እየተወራጩ ነ. ው?!ጥ. ሩ ታዲያ ምን አለ የሰሞኑ ጥያቄያችሁ ሁሉ

ከዚህ … ከዚህ ከእናቴ ላይ እየወጣና እያናጠረብኝ ሰ.ለ.ሆ.ነ … አባታችሁም

ይ.ም.ጣ.ና እንነጋገርበታለና!!

# ትዕይንት አምስት

5. ከዚያው ቤት ሳሎን - ማታ ላይ

5.1 በጅምሩ የቤቱ የውጪው ገጽታ ማታ ላይ

የበረንዳው መብራት እንደ በራ ይ.ታ.ያ.ል

5.1.1 የቤቱ ገጽታ እየታየ ከሳሎኑ ውስጥ የአቶ ማሩ እና የወ/ሮ ጌጤ ሳቅ ይሰማል

5.1.2 ያልተዘጋው የሳሎኑ መስኮት ከርቀት እየቀረበ ይታያል

5.2 ከሳሎኑ ውስጥ

5. ከሳሎኑ ውስጥ ካሉት አሮጌ ሶፋዎች ላይ ከትልቁ ሶፋ ላይ ወላጆቹ ጎን ለጎን

ተቀምጠው እየሳቁ ከነሱ ፊት ለፊት ደግሞ ልጆቹ እንደ ተጨበጡ ተቀምጠውና

አቀርቅረው ሲያዳምጡና ሲያስቡ ይታያሉ፡፡

አቶ ማሩ - ሳቃቸውን እየጨረሱ እ.ው.ነ.ቴ.ን እኮ ነው

ወ/ሮ - ሳቃቸውን እየጨረሱ እኮ ታዲያስ!!

ማሩ - አዎን - እንደዚያ ማለቴ ገ.ነ - ለምን ጥ.ሩ -ጥ.ሩውን ሁላ ለመመገብ አ.ሰ.ባ.ች.ሁ ወይ ደግሞ ለምን ጥሩ ጥሩውን እየለበሳችሁና እያሸበረቃችሁ ለመታየት ተመኛችሁ ማላቴም አይደል!!

ጌጤ - አ.ዬ ጥሩ ጥሩውን በመመኘት እሚገኝ ቢሆንማ ኖሮ ማን ይጠላዋል?!

ማሩ - ስነግርሽ! አሁን ማን ይሙት እኔስ እራሴስ ቢሆን እንዲህ እንደ ጓደኞቻችሁ አባት ያላቸውን መኪና ገዝቼና ይገፍ በዚህ በሰፈራችን ሰዎች መሀል ጥሩንባይቱን እያንደቀድኩኝ ሽው እልም እያልኩኝ በጎዳናው ላይ መካነፋን የምጠላው መሰላችሁ!?

ጌጤ - የማሩን የመጨረሻ ንግግር በመታከክ እኔስ ብ.ሆ.ን እንዲህ እነ መዓዛ እናት ( እንደ ጎረቤት) ጸጉሬን እየተተኮስኩና እየተተ.ተ.ተፈፍሽነ.ኩ

ኤደን - የማፈር ሳቅ እየሳቀች ኧ/ረ እ.ማ.ዬ...

ጌጤ - እና ሃዲያ ይ. ሄ ይሄ ደግሞ ምን ነበር የከንፈሩ...

ማሩ - ምን ሊ.ሊ.ብ.ስ.ቲካ...?

ጌጤ - አዎን ሊቢስትካዬ እየተለቀለቅሁኝ ይሄን ታኮ ጫማዬን ግድግድ አድርጌ ቂ.ን.ቂ.ን. እያልኩኝ ካልሄድኩኝ እ.ያ.ል.ኩ.ኝ

ማሩ - አቋርጧቸው በ.ለ.ው!! በይ በይ እናቴ እንዲህ ዓይነቱን ምኞት ብትምኝልኝ አይሻልሽም እንጂ ቢሻልሽስ የዛን ጊዜ እኔ ማሩ ይሄን ቤት ብቻም ሳይሆን ይሄን ሰፈሩን ጥዬልሽ ወደ ጫካ ነወ የምሸፍተው!!

ወ/ሮ ጌጤ - ም.ም ምሳሌውን እኮ ነው!

ማሩ - ቢሆንም - ቢሆንም ጌጤ -- እኛ እነዚህን ልጆች ሳይቀር ይሄን ሁሉ ዘመን በፍቅርና በሰላም ለመኖር የበቃነው ካቅማችን በላይ ያለውን ሁሉ እየተመኘንና ከሰው በታች ሆነናል በሚል እየተቆጨን ሳይሆን "ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አያድርም" እንደሚባለው የአባቶች ተረት በአቅማችን ልክ እያመጣጠንን እና ያለንን እያጣጣምን በመደሰታችን ሰዓት ልጆቼ እ.ና.ን.ተ.ም የጎረቤታችንን ኑሮ ለራሳቸው

እየተዋችሁላቸው እንደ ቤታችን እንኖራለን ብላችሁ የራሳችሁን ይዛችሁ ብታጣጥሙት ይሄ ዛሬ የምትመኙትን ሁሉ ጠንክራችሁ ከተማራችሁ ነገ ሠርታችሁ የምታገኙት ስለመሆኑ እርግጠኛ ሆኜ ነው የምነግራችሁ፡፡

ልጆቹ ከተቀመጡበት ተነሰ.ተው ሄኖክ ወደ እናታቸው ኤደንም ወደ አባቷ ሄዳ ጉልበት ይስማሉ፡፡